DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

GOVERNMENT OF THE
DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

Early Childhood
DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# ቢውልዲንግ ብሎክስ (Building Blocks) የሚባለውን የሂሳብ ሥርዓተ-ትምህርት ማስተዋወቅ!

## ሰላም የ ዲሲፒኤስ የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት (Pre-K) ቤተሰቦች!

ስለመጪው የትምህርት ዘመን ደስተኛ እንደሚሆኑ ተስፋ እናደርጋለን! በቅድመ-መዋዕለ ህጻናት (Pre-K) የትምህርት ስርዓታችን ላይ ስለሚደረጉ አንዳንድ ለውጦች መረጃ ልናካፍልዎ ጓጉተናል። ከ2023-2024 የትምህርት ዘመን ጀምሮ በሁሉም የቅድመ-መዋዕለ ህጻናት ትምህርት ክፍሎቻችን ቢውልዲንግ ብሎክስ (Building Blocks) የሂሳብ ስርዓተ-ትምህርትን እናስተዋውቃለን። ከዚህ በታች ስለዚህ ይህንን ሥርዓተ-ትምህርት በሚመለከት አንዳንድ የተለመዱ ጥያቄዎችን እንመልሳለን።

## ሂሳብ ለምን?

በለጋ የልጅነት አመታት ውስጥ በሂሳብ ውስጥ ጠንካራ መሰረት ያዳበሩ ልጆች በአንደኛ ደረጃ እና ከዚያም በላይ በሒሳብ የበለጠ ስኬታማ ይሆናሉ። እንዲሁም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመፃፍ እና በሌሎች ጠቃሚ ክህሎቶችም የተሻሉ ናቸው። **በሌላ አነጋገር፣ ቀደምት የሂሳብ አስተሳሰብ እና ትምህርት በልጆች በሂሳብ፣ ማንበብና መጻፍ እና ሌሎች አካዳሚክ ትምህርቶች ስኬት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።**



*የዲዲፒኤስ (DCPS) ቅድመ-ትምህርት ምሁር የመጨወቻ ሊጥ በመጠቀም የ "ከፊል-ለ-ሙሉ" ('part-to-whole') ግንኙነቶችን እያሰሰች ነው። ከፊል-ወደ-ሙሉ ውይይቶች የልጆችን የክፍልፋዮች ቀደምት ጽንሰ-ሀሳብ ይደግፋሉ።*

## ቢውሊዲንግ ብሎክስ (Building Blocks) ለምን?

ቢውልዲንግ ብሎክስ *(Building Blocks)* ህጻናት ቀደምት የሂሳብ ክህሎቶቻቸውን በተግባር እና በጫወታ የመማር ልምድ እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል። ሒሳብ የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለት ሕይወት አካል እንደሆነ እናምናለን፣ ስለዚህ በልጅዎ የዕለት ተዕለት ልምድ ውስጥ የተካተተ መሆኑን እርግጠኛ እንሆናለን።



ቢውልዲንግ ብሎክስ *(Building Blocks)* የሂሳብ ሥርዓተ-ትምህርት ከዲሲ የቅድመ-ትምህርት ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ እና በሂሳብ ትምህርት ውስጥ **ስድስት** የተለያዩ ዘርፎችን ይሸፍናል።

## የቅድመ ትምህርት ተማሪዎ የሚከተሉትን ይመረምራል:

1

**ቁጥርን ማወቅ፤**
ልጆች ቁጥሮችን እንዲረዱ እና እርስ በርስ እንዴት እንደሚገናኙ እንዲረዱ ለመርዳት የታቀደ እስደሳች ስራዎች አሉን። ለወደፊት የሂሳብ ስኬታቸው መሰረት እንደመጣል ነው።

2

**ተግባራት፤**
ለወደፊት ውስብስብ ስሌቶች ጠንካራ መሰረት መገንባት እንፈልጋለን።

3

**የዳታ (Data) ትንተና እና ምደባ፤**
ልጆቻችሁመረጃንእንዴትእንደሚ ሰበስቡ፣እንደሚያደራጁእናእንደ ሚተረጉሙበማስተማርወደየዳታ አለምውስጥእንገባለን። እጅግ በጣም ጥሩ ትንታኔ ሰጪዎች ይሆናሉ።

4

**አደረጃጀት (Patterns) እና አልጀብራ (Algebra)፤**
ሒሳብን የበለጠ አስደሳች የሚያደርጉ እንደ እንቆቅልሽ የሆኑ አደረጃጀቶችን፣ ቅደም ተከተሎችን እና ግንኙነቶችን እንመረምራለን። ለወደፊት ችግር አፈታት መሰረት ነው!

5

**መለኪያ (Measurement)፤**
መጠንን፣ ክብደትን፣ ርዝመትን እና ስፋትን ለማወቅ ይዘጋጁ! ትናንሽ ልጆቻችሁ ስለ መለኪያዎች እና በእውነተኛ ህይወት ሁኔታዎች ላይ እንዴት እንደሚተገበሩ ይማራሉ።

6

**ጂኦሜትሪ (Geometry)፤**
በተግባራዊ ልምድ እና አሰሳ፤ የህጻናት የቦታ ማመዛዘን ችሎታን ያዳብራሉ፤ እና ስለቀጾች እና ልዩ ባህሪያቶቻቸው ይማራሉ።



## ቢውልዲንግ ብሎክስ *(Building Blocks)* ብጨኛው ጥቅም ላይ የሚውል ስርዓተ-ትምህርት ይሆናል?

አይ! በዲሲፒኤስ (DCPS) በልጅ ሁለንተናዊ ትምህርት እናምናለን፤ በተለይም በለጋ የልጅነት እድሜ ጊዜ። የቅድመ-ትምህርት ክፍሎቻችን የልጆችን ቋንቋ፣ ማንበብና መጻፍ፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ ችሎታዎች እና ሌሎች ክህሎቶችን በጨዋታ እንቅስቃሴዎች ለማዳበር የተነደፉ ናቸው። እንዲሁም ቢውልዲንግ ብሎክስ (Building Blocks) “ሁለተና ልጅ” ("whole-child") አካሄድን ይከተላል፤ አወንታዊ የሆነ አካባቢ ለመፍጠር በአስተማሪ የሚመሩ ተግባራት፣ የማስመሰል ጨዋታ፣ ማራኪ ዘፈኖች እና አስደናቂ ታሪኮችን በማካተት!

ከቢውልዲንግ ብሎክስ *(Building Blocks)* ጀርባ ስላለው ምርምር ማወቅ ጓጉተዋል? የበለጠ ለመማር *learningtrajectories.org* ን ይጎብኙ

dcps.earlychildhood@k12.dc.gov
DCPS Early Childhood Education
@dcpsearlychildhood